# ማውጫ


ገጽ

ርዕሰ አንቀጽ 2

የአስተዳደር ቦርድ መልእክት 4

የትምህርት ኮሚቴ መልእክት 6

የሀመረ ኖህ ሰንበት ት/ቤት 7

አባት መዘምራን 11

የእናቶች ማህበር 12

ወይብላ ማርያም ማህበርተኞች 13

## የበረከት ወንጌል አምድ

- የዓለም ድኅነት 14
- ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ 17
- አገልግሎትና አገልጋይ 24
- **The Biblical Ethiopia** **31**

## መንፈሳዊ ግጥሞች

- ዝምታ 35
- እረኛው 36

# ርዕስ አንቀጽ

## መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ የሀበነ ሰላመ፣

የጌታን ወደዚህ ዓለም መምጣት ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችን ሰፋ አድርጋ ስትገልጥ ዓለምን ይቤዥ ዘንድ መጣ፣ ደግሞም ሰላምን ይሰጥ ዘነድ ስትል ቀዋሚ ዓላማዎቹን ትናገራለች።

አንድ አስተዳዳሪ ወይም ባለሥልጣን ከክፍለ ሀገሩ ወደ አንዱ ክፍለ ሀገር፣ አውራጃ ወረዳ ሲሄድ ግብር ለማስገበር ብዙ ወጭን ለማስወጣት በተገዥዎች ላይ የጭቆና ሥራን ለማሳየት ነው እንጂ ለሌላ ነገር አይሄድም።

በቀድሞው የገዥዎች ጉዞ አንፃር ስንመለከተው ደግሞ ገዥው አስተዳዳሪው ወደ ልዩ ልዩ ክፍለ ግዛቱ ሲሄድ መንገዱ እንዲደለደል፣ ኮረብታው እንዲስተካከል፣ ጎድጓዳው እንዲሞላ በጠቅላላው ለእርሱ ምቾት የሚሰጥ መንገድ እንዲሆንለት የጭቆና ሥራን ይሠራል። ይኽ ሁሉ ባይደረግ ደግሞ አገሩ እንዳመፀ ተቆጥሮ መቀጮ ይጣልበታል፤ ስለዚህ ወዶ ፈቅዶ ይኽን አድካሚ ሥራ ሠርቶ መፈጸም ፣ የተጣለበትንም ዕዳ ከፍሎ መቆየት አለበት።

ክርስቶስ ግን ወደኛ ሲመጣ የተጣለብንን ዕዳ ለማንሳት የጠመመውን ለማቃናት የጎደለውን ለመሙላት ስለሆነ ዓለምን ይቤዥ ዘንድ መጣ፣ ሰላምንም ይሰጠን ዘንድ መጣ አለ። ቤዛ መሆን ፥

1. ለከፍተኛ ባለ ዕዳ ዋስ ሁኖ ታስሮ እንደሆነ ማስፈታት፤ ተከሶ እንደሆነ ፋይሉን ማዘጋት ቤዛ መሆን ነው፤ ለባለዕዳው ተለዋጭ ሁኖ መግባት ነው።
2. ቤዛ ብዙ ዕዳ ተጥሎበት ሁሉንም ለመክፈል አቅቶት እርሱም ሚስቱም ልጆቹም ተሸጠው እንዲከፍሉ፣ ያለዚያም ለዘለዓለም ታስረው እንደሆን ለተፈረደበት ቤተሰብእ ቤዛ ሁኖ ማዳን በዚህ ዕዳ ተጠያቂ ነኝ ብሎ ገብቶ ገንዘቡን መክፈል፣ ያለዚያ በሰውየው ቀንበር እርሱ ገብቶ ነፃ መውጣት ቤዛ መሆን ይባላል።
3. እስከሞት የሚደርስ ዕዳ ችግርም ቢኖር ለባለዕዳው ተለዋጭ ሁኖ ቤዛ ሁኖ መግባት መሞት ቤዛነት ነው።
4. በጠቅላላው ባለ ዕዳውን አድኖ በእርሱ እግር ገብቶ መሞት ቤዛነት ነው።

እንግዲህ መድኃኒታችን ኢየሱስ በኛ ዕዳ ገብቶ የኛን ሞት እርሱ ሙቶ የእርሱን ሕይዎት ለኛ ስለሰጠን ቤዛችን ተለዋጫችን ሁኖናል።

ክርስቶስ ለኛ ቤዛ ሲሆን በሚያልፍ በሚጠፋም በብርና በወርቅ አልተቤዠንም ነገ ግን የከበረ ደሙን በማፍሰስ በደሙ ገዛን፥ በደሙ ነፃ አወጣን እንጂ። ይኽንም ቅዱስ ጴጥሮስ ሲገልጥ

«ታውቃላችሁና በሚጠፋ በወርቅና በብር ከከንቱ ሥራችሁ እንዳልዳናችሁ፣ ካባቶቻችሁ ከተቀበላችሁት ነገር ግን በከበረው በበግ ደም ነውር ርኩሰትም በሌለበት እርሱም ክርስቶስ» (፩.ጴ. ፩፥፲፰-፲፱)

ሲል በሰፊ ያስረዳል። የሀበነ ሰላመ፣ ሰላምን ይሰጠን ዘንድ ሰው ያጣው በግድም ሊኖረው የሚገባው ሰላም ነው።

ከማንኛውም ስጦታ ሰላም አንደኛው ስለሆነ ክርስቶስ ሲወለድ ያናገረው ሰላም ለምድር በማለት ነው (ሉቃ.፪፥፲፬)። ሰላም በምድር በሰማይም በኅዋውም፣ በልዩ ልዩ ፕላኔቶችም ሰላም ይሁን አላለም ምክንያቱም የጠፋው ሰላምም የሚያስፈልገው መሬት ነው ወንጌላዊው ዮሐንስ በራእዩ እንደተናገረው ዲያብሎስ ወደመሬት ከወረደ ወዲህ መሬት ችግር አለባት፣ ሰላም ጠፍቶባታል ችግር በዝቶባታል። እርሱንም እንዲህ ሲል ይገልጣል

«ስለዚህ ደስ ይበላችሁ እናንተ ሰማያት በእርሳቸውም ያላችሁ። በምድርና በባህር ለምትኖሩ ግን ወዮላችሁ ዲያብሎስ ወርዶባችኋልና በእርሱም ታላቅ ቁጣ አለበት ጥቂት ዘመን እንደቀረለት ያውቃልና»። (ራእይ.፲፪፥፲፪) ።

ክርስቶስ የመጣው በምድር ሰላምን ለመመሥረት ነውና። እርሱ ራሱ የሰላም አለቃ፣ ሰላም የሚገኘው ከእርሱ ነውና። ኢሳይያስ የሰላም አለቃ ብሎ ሰይሞታል (ኢሳ. ፱፥፮)። ራሱ ክርስቶስ ሲያስተምር

«ሰላምን እተውላችሁአለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችሁአለሁ....»(ዮሐ.፲፬፥፳፯)።

ሲል ራሱ ሰላም ስለሆነ እሰጣችሁአለሁ አለ። ክርስቶስ ከሙታን ሲነሳ ለመጀመሪያም የሰጠው ቃል ሰላም ለሁላችሁ ይሁን የሚለውን ነው። መላልሶም የተናገረው ቃል ሰላም ለሁላችሁ ይሁን የሚል ነው፣ ይኽም ማለት ለሁላችን የሚያሻን ሰላምን ማግኘት ነው የክርስቶስ መስቀል የሰላም ዓርማ ነው ራሱ ክርስቶስ የሰላም ንጉሥ ነው ለኛም የሚያስፈ ልገን ሰላም ነው፣ ስለዚህ የሰላምን አለቃን እንከተለው።

ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ

# የመካነ ሰላም መድኃኔዓለም ካቴድራል

# አስተዳደር ቦርድ መልእክት

በክርስቶስ ክርስቲያን የተባላችሁ ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች በቅድሚያ እንኳን ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ዓመታዊ የመድኃኔዓለም (ጥንተ ስቅለቱ ) በዓል በሰላም በጤና አደረሳችሁ፣ አደረሰን እያለ የመካነ ሰላም መድኃኔዓለም ካቴድራል አስተዳደር ቦርድ መልካም ምኞቱን ይገልጻል

የተወደዳችሁ የጌታችን የመድኃኔዓለም ቤተሰቦች ፤ ይህ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደተቋቋመና እንደተመሠረተ ወደኋላ መለስ ብለን በምናስታውስበት ጊዜ፤ በመጀመሪያ በጥገኝነት በግሪኮች ቤተ ክርስቲያን ሲሆን፤ በዚያ በነበርንበት ጊዜ የመውጫና የመግቢያችን ሰዓት የተወሰነ በመሆኑ ተሸማቀን ያሳለፍነው ጊዜ የሚረሳ ባይሆንም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዕርዳታ ስለአልተለየን የራሳችን የሆነ ቤተ ክርስቲያን ለምን አንገዛም በማለት በአደረግነው ውሣኔ ፣ ጥንካሬና መረባረብ በርክሊ የሚገኘውን ቤተ ክርስቲያን ገዝተን በዚያ ለ15 (አሥራ አምስት) ዓመት ስንገለገል ቆየን።

በኋላ በየጊዜው የምእመናን ቁጥር እየጨመረ በመሄዱና ቤተ ክርስቲያኑም በመጥበቡ የገዛንበትን $300,000 (ሶስት መቶ ሺህ ዶላር) እስክንጨርስ ድረስ ለጊዜው በዚያ ስንገለገል ቆየን። ዕዳችን እንዳለቀ በአደረግነው ጥናት ባዶ መሬት ገዝተን ሰፋ ያለና የተሟላ ዝግጅት ያለው ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት አሰብን። ይህንኑ ሃሳባችንን ለምዕመናኑ አሳውቀን ሙሉ ድጋፍ በማግኘታችን ከባንክ $390,000 (ሦስት መቶ ዘጠና ሺ ዶላር) ተበድረን መሬት ገዝተን አዲስ የሚሠራውን ቤተ ክርስቲያን ፕላን በማሠራት ከፍተኛ ጥረት በምናደርግበት ጊዜ ፤ ምዕመናን ከጎናችን በመቆም ለቤተ ክርስቲያኑ ማሠሪያ ገንዘብ ቢያዋጡም የሚያስፈልገው ገንዘብ ከፍተኛ በመሆኑ በቅርብ ጊዜ ተሠርቶ ልንገለገልበት የማንችል መሆናችንን ከመረዳታችንም ባሻገር ፤ የምዕምናኑም ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሄዱ በነበርንበት በርክሊ ቤተ ክርስቲያን መቆየት አልቻልንም። ከዚህም የተነሳ ይኸንን ችግራችንን በቅርብ ማቃለል የምንችልበትን መንገድ ስንፈልግ ያገኘነው የመፍትሔ ሃሳብ ሰፋ ያለ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ገዝተን ለጊዜው ተገልግለንበት

የገዛንበትን ዕዳ ስንጨርስ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ማሠራት ሲሆን ይህን የመፍትሄ ሃሳብ ለምዕመናኑ አቅርበን ሙሉ ድጋፍ በማግኘታችን አሁን ያለንበትን ቤተ ክርስቲያን በ$3,500,000 (ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ዶላር) ገዝተን እግዚአብሔር ስሙ ይባረክ ይኸው በመገልገል ላይ እንገኛለን። ይህንንም ልንፈጽም የቻልነው በእናንተ ተብብርና እርዳታ በመሆኑ ወደፊትም ድጋፋችሁ እንዳይለየን እንጠይቃለን።

ከዚህም ሌላ ቦርዱ ያከናወነው የቤተ ክርስቲያኗ አገልጋይ የሆኑት አባቶች የሚኖሩበት ቦታ የራቀና የተነጣጠለ በመሆኑ ችግር በማስከተሉ አዲስ በገዛነው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉንም የሚያኖር ክፍል ባለማግኘታችን ችግሩን ለማቃለል በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ የሚሸጥ ቤት በመገኘቱ ከባንክ ተበድረን ገዝተን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

አሁንም ያለብን የብድር ገንዘብ በእናንተው ትብብር ተከፍሎ በሚያልቅበት ጊዜ የተገዛውን ቦዶ ቦታ እንዴት መገልገል እንደምንችል አጥኚ ኮሚቴዎች በሕዝቡ አሜንድመንት የተቋቋመ ስለሆነ ኮሚቴው የሚያቀርበውን ሃሳብ ተመልክተን አስፈላጊውን ለመፈጸም በዝግጅት ላይ እንገኛለን።

የአስተዳደር ቦርዱ ቤተ ክርስቲያኑ የተገዛበትን የብድር ገንዘብ (ሞርጌጅ) ለመክፈል የምዕመናኑን እርዳተ በመጠየቅና ፈንድሬዚንግ  በማድረግ የሚያሰባስበውን ገንዘብ ለሞርጌጅ ክፍያ ለባንክ በየጊዜው በመስጠት ዕዳው የሚቃለልበትን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው። በየጊዜው ከምዕመናን የሚሰበሰበውንም ገንዘብ በወርና በየሦስት ወር የሂሳብ ሪፖርት ለምዕመናን በማቅረብና በማሳወቅ ምዕመናን የተለመደ ትብብራቸውን እንዲያደርጉና ያለብንን ዕዳ ከፍለን እንድንጨርስ በማሳሰብ ላይ ይገኛል።
በቤተ ክርስቲያኑ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከምዕመናኑ ልዩ ልዩ ፮ ንዑሳን ኮሚቴዎችን አቋቁሞ የዕለት ተዕለት ሥራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

በመጨረሻም ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ጉልበታችሁን ጊዜያችሁንና ገንዘባችሁን የሰጣችሁትን እና እየሰጣችሁ ያላችሁትን አባሎችና ደጋፊዎች ከልብ እያመሰገንን፤ ለመድኃኔዓለም በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ በማለት ሰላምንና ጤንነትን ሰጥቶን አንድነታችንን

ጠብቆ ለሚቀጥለው ዓመት እግዚአብሔር በሰላም ያደርሰን ዘንድ መልካም ምኞታችንን እንገልጻለን።

የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን !

# የትምህርት ኮሚቴ መልእክት

## የትምህርት ኮሚቴ ከየት ወዴት?

የክርስትና እምነት ህልውናውና መሠረቱ የእግዚአብሔርን መኖር ማወቅና ሕያው በሆነው እግዚአብሔር ማመን ስለሆነ፣ የተዋህዶ እምነታቸን በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት በተለያዩ ጊዜያት በተጻፉ ቅዱሳን መጻሕፍት የተገለጠ አምላካዊ ክስተት እንጂ በመመራመር የሚገኝ ፍልስፍና ወይም በዘር ሐረግ የሚወረስ ርስት ባለመሆኑ እያንዳንዱ አማኝ ቅዱሳት መጻሕፍትን መመርመርና ማጥናት እንዲሁም ክአባቶቻችን የተላለፈውን ትዉፊት ማወቅና መጠበቅ ይኖርበታል።

በተለያዩ የዕድሜ ክልልና የትምህርት ደረጃ ለሚገኙ ምዕመናን በየደረጃቸው በተለያየ ስልት ተዘጋጅቶ በመደበኛነት የሚሠጥ የተጠናከረ ክርስቲያናዊ ትምህርት ባላመኖሩ፣ ምዕመናን እምነታቸውን ጠንቅቀው ካለማወቃቸው የተነሳ በቤተክርስቲያን ጸንተው እንዳይቆሙ በቀላሉ የመታለልና የመኰብለል ሁኔታ በተደጋጋሚ ሲያጋጥም በማየታችን፣ የቤተ ክርስትያናችንን እምነትና ትምህርት ከሚያጥላሉና ከሚነቅፉ ወገኖች ጋር ምዕመናን ከመተባበር እንዲገቱ ለማድረግ እንዲቻል፣ እንዲሁም የተዋሕዶ እምነታችን የቱን ያህል በቅዱሳት መጻሕፍት አስረጂነት የተደገፈ መሆኑን በግልጽ ማስተማር የቤተክርስቲያን የወቅቱ ጥሪ መሆኑን ተገንዝበናል።

ከላይ የተገለጹትን እውነታዎች ዕውን ማድረግ የሚቻለው በቤተክርስቲያን አባቶች ምክርና አመራር ላይ የተመረኮዘ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚካሄዱ ማናቸውም ትምህርት ነክ ጉዳዮች ሀላፊነት ወስዶ ችግሮችንና የመፍትሔ ሀሳቦችን እያጠናና እየመረመረ ለቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ (ቦርድ) በማቅረብ ውሳኔ የሚያሰጥ፣ በቤተክርስቲያን ቃለ ዐዋዲ መሠረት የሚመራ አንድ አካል ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበትና ሁሉም ነገር በአግባቡና በሥርዓት እንዲከናወን በማሰብ (1ቆ.14፥40) በመካነ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተጠሪነቱ ለሰበካ ጉባዔው (ቦርድ) እና ለመንበረ ጵጵስና በሆነው መንፈሳዊ አገልግሎት ሥር የተጠናከረ የትምህርት ንዑስ ኮሚቴ በአዲስ መልክ ተዋቅሮ ሥራውን ከጀመረ ወራቶች አስቆጥሯል። ይህ ኮሚቴ በፊት ሥራው ያከናውን ከነበረው ኮሚቴ የሥራ መመሪያ ተቀብሎ ከማራመድ በተጨማሪ ከልምድ በተገኙ ተመክሮዎች ነገሮችን በመጨመር በሥራ ያልዋሉትን በመቀነስ ሰባት አመራር አባላትን ሰይሞ ተግባሩን በማከናወን ላይ ይገኛል። በዚሁ መሠረት

1ኛ/ የቤተክርስቲያናችንን እምነት፣ ሥርዓትና ታሪክ ለምዕመናን በማስተማርና በማሳወቅ ላይ ይገኛል።

2ኛ/ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ሥርአት መሠረት በሰንበትና በበዓላት ቀናት ለምዕመናን የስብከት ትምህርት እንዲሁም የመጻሐፍ ቅዱስ ጥናት ለሕፃናት፣ ለወጣቶችና ለአዋቂዎች በማዘጋጀት እያስተማረ ይገኛል።

3ኛ/ የሰንበት ትምህርት ቤት ታዳጊ ሕፃናት የእናት አገራቸውን ቋንቋ እንዲናገሩ እንዲሁም የቤተክርስቲያናቸውን ዶክትሪንና መሠረታዊ መጽሐፍ ቅዱስ ሊያውቁ የሚችሉበትን ዘዴ ዘወትር እሁድ ጠዋት በበጐ ፈቃደኛ መምህራን በተጠናከረ ሁኔታ በመስጠት ላይ ይገኛል።

4ኛ/ የቅዳሴ ዜማዎችንና መንፈሳዊ የአማርኛ መዝሙሮችን በካሴትና በሲዲ በማዘጋጀት እንዲሁም ዘወትር በቅዳሴ ሥርዓት ምዕመናን እንዲሳተፉ እያደረገ ይገኛል።

5ኛ/ አበው ሊቃውንትን መንፈሳዊ መምህራን በመጋበዝ ጉባዔዎችን በማዘጋጀት ምዕመናን በመንፈሳዊ ዕውቀት እንዲበለፅጉ በማድረግ ላይ ይገኛል።

በአጠቃላይ ይህ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ዶክትሪን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ሥነ ምግባር፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ የግዕዝ ቋንቋ መግቢያ፣ የዜማ ትምህርት፣ የቅዳሴ ትምህርት፣ የኢትዮጵያ ፊደልና የቋንቋ ትምህርት እንዲዘወተሩ በማድረግ ይረዳል፤ ያስተባብራል፤ ይመራል።

# የሐመረ ኖህ ሰንበት ት/ቤት

*"ምንም አንኳ በለስም ባታፈራ፥በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥የወይራ ሥራ ቢጎድል፥እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በመድሃኒቴ አምላክ ሐሴት አደ ርጋለሁ።"* ትንቢተ እንባቆም 3፥ 17-18

የሐመረ ኖህ ሰንበት ትምህርት ቤት ከተቋቋመ እነሆ 15 ዓመት ያለፈው ሲሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሰንበት ትምህርት ቤቱ መንፈሳዊ እድገትም እያደገ መጥቷል። በዚህ ጊዜ ውስጥም የሰንበት ት/ቤቱ ይህ ነው የማይባል መንፈሳዊ አገልግሎትን በማከናወን ላይ ይገኛል። ዋነኛው አገልግሎት መንፈሳዊ መዝሙር በየሳምንቱ የማቅረብ አገልግሎት ሲሆን፤ ከዚህ ሌላ ማህበሩ በገንዘብ ማሰባሰብ፣ መንፈሳዊ ጉባኤዎችን በመካፈል፣ አጫጭር ድራማዎችን በማዘጋጀት፣ በየ፫ ወር የሚወጣ ጋዜጣንና የተለያዩ መንፈሳዊ ዝግጅቶችንም በማድረግ ለቤተክርስቲያኗ ታላቅ አገልግሎት ያበረክታል።

<u>በዓመት ውስጥ የተከናወኑ ፕሮግራሞች</u>

- ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ/ም (11-20-2008) የሐመረ ኖህ የሰንበት ትምህርት ቤት «የምስጋና ቀን» በማለት ባዘጋጀው ልዩ ፕሮግራም ላይ በርከት ያሉ ምዕመናን በተገኙበት በዓሉን በታለቅ ድምቀት ያከበርን ሲሆን በዚህም ምሽት ምዕመናኑ አምላካቸው የፈጸመላቸውን (ያደረገላቸውን) ታምራት በመናገር ታላቅ የምስክርነት ቃል የሰጡ ሲሆን በምሽቱም

ምዕመናን ያሬዳዊ መዝሙሮችን በህብረት በመዘመር ለፈጣሪያቸው ምስጋና ያቀረቡበት ምሽት ከመሆኑም ሌላ በየመዝሙሮቹ መሀከልም የመጽሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ከምእመናን ውስጥ በተወጣጡ ሰዎች ይነበብ ነበረ። በመጨረሻም የጧፍ ማብራት ሥነስርዓት በማድረግ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ። በዚህ ምሽትም ቁጥራቸው በርከት ያሉ ምዕመናን ይህ የምስጋና ቀን በየ፫ ወር እንዲደረግ ጠይቀዋል።


- የሰንበት ትምህርት ቤቱ በዚህ በያዝነው ዓመት ካከናወናቸው መንፈሳዊ ተግባራት ውስጥ ቋሚ እና መደበኛ የሆነ በየ፫ ወር የሚትወጣ አራራት የተሰኘች አነስተኛ መንፈሳዊ ጋዜጣ እያዘጋጀ በማቅረብ ላይ ሲሆን ይህቺ ጋዜጣ ገጹ አነስተኛ ቢሆንም በውስጡ ግን ይህ ነው የማይባል ይዞታና ጠቀሜታ ያላት ሲሆን የሰንበት ትምህርት ቤቱን እንቅስቃሴ የሚያሳይ፣ መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጡ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ጽሁፎች በማቅረብ፣ ምዕመናኑን የሚያሳትፍ መንፈሳዊ ጥያቄና መልስ የያዘ ጽሁፍና የቤተክርስቲያናችንን ወቅታዊ የሆኑ መርሃ ግብር የያዘ ጽሁፍ አዘጋጅቶ ለምዕመናኑ በጋዜጣ መልክ በነጻ እያቀረበ ይገኛል።

- ባሳለፍነው ዓመትም የሰንበት ትምህርት ቤቱ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ የገቢ ምንጭ የሆነውን የመኪና ማጠብ ፕሮግራም ፈቃደኛ ከሆኑ ምዕመናን ጋር በመሆን በአዲስ የኢትዮጵያ ሬስቶራንት በማድረግ ለቤተክርስቲያናችን 7227 ዶላር አሰባስቦ ለቤተክርሰቲኗ ገቢ አድርጓል

- ለቡሄ ዓመታዊ በዓል እንደተለመደው ለየት ያለ መንፈሳዊ ጭውውት፣ ስነጽሁፎችን በአርቲስት ተስፋዬ ሲማ አዘጋጅነትና አሰልጣኝነት ምዕመናኑን እያዝናና መንፈሳዊ ትምህርት የሰጠ ዝግጅት አቅርቦ 2 ሺ ዶላር ገቢ ለቤተክርስቲያኑ አስገብቷል።

- እንዲሁም ሰንበት ትምህርት ቤቱ ባለፈው ዓመት በፆም ወቅት የበገና መሳሪያ ተጫዋችና ዘማሪ የሆነውን ተመስገንን በማስመጣት በጽርሐ ጽዮን አዳራሽ ዝግጅት በማድረግ 9704 ሺ ዶላር ገቢ ለቤተክርስቲያኑ አድርጓል።

በተጨማሪም ይህ የወጣቶች ሰንበት ትምህርት ቤት የመቅደሱን የጽዳት አገልግሎት




MZ Meseret Y. Zeleke, Certified Public Accountant

Meseret Y. Zeleke

337 37th Street

Richmond, California 94805

(510) 232-1117 • FAX (510) 232-1345

E-mail: meserety@aol.com


CAFE DAREYE
ካፌ ዳርዬ
AUTHENTIC ETHIOPIAN DELICACIES
2504 Telegraph Avenue Oakland, CA 94612
Tel. (510) 286-1900
Open 7 Days a Week for Breakfast, Lunch, and Dinner
We Cater for Weddings and Special Events
At Café Dareye we use our Family recipe with the Best imported and Traditionally seasoned Herbs and Spices


ARADA GEBEYA
510.547.8332
Oakland, Ca 94609
5711 Telegraph Ave.
Get Your Products Straight from Afrika:
- Ethiopia, Nigeria, Kenya, Ghana & Senegal -
Traditional AfrikanAttire/Arts & Crafts/
Jewelry/Clothing/MetroPCS
aradagebeya@sbcglobal.net

በሀላፊነት በመውሰድ ከአንዳንድ ምዕመናን ጋር በመሆን በየሳምንቱ የጽዳት አገልግሎት በማድረግ በተገቢው መንገድ ያጸዳል እንዲሁም ከዚህ በረከት ለመቋደስ የሚፈልጉትን ሁሉ የሰንበት ትምህርት ቤቱ በፍጹም ደስታ ይቀበላል። ከዚህም በመቀጠል ይህ የወጣቶች የሰንበት ትምህርት ቤት ከያዛቸው ፕሮጀክቶች ውስጥ አንዱ በዚህ በያዝነው ዓመት ለመድኃኔዓለም ጥንተ ስቅለት በዓል አዲስ የመዝሙር ሲዲ አዘጋጅቶ ማቅረብ ሲሆን ዝግጅቱም ተጠናቆ እስቱዲዮ ተቀድቶ አልቆ የበዓሉ ቀን ለሽያጭ ይቀርባል። የሰንበት ትምህርት ቤቱ ለአዳዲስ ወጣት መዘምራን በሩ ክፍት ሲሆን በማንኛውም የሰንበት ቀን መጥተው የሚመለከታቸውን የሰንበት ትምህርት ቤት አባላት ማናገር ይችላሉ።

በመጨረሻም ከዚህ በላይ የተገለጹትን የጉልበት አገልግሎትም ሆነ የገንዘብ ማሰባሰቡን ስናደርግ ሁል ጊዜም ለማይለየንና በነገሮች ሁሉ ለረዳን ለቸሩ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና እያቀረብን በመቀጠልም ለዚህ ሁሉ ተሳትፎ እንድንበረታና ለሰንበት ት/ቤቱ ሞራልና እድገት በመስጠትና ከምንም በላይ ደግሞ በምናዘጋጀው ዝግጅት ሁሉ ጥሪያችንን በማክበርና ገንዘባችሁን በማውጣት ለቤተክርስቲያኑ ገቢ በማድረግ ለተባበራችሁን የመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን አባላትና ምዕመናን ዋጋችሁን መድኃኔዓለም ይክፈላችሁ እያለ የሐመረ ኖህ የሰንበት ትምህርት ቤት ምስጋናውን ያቀርባል።

የሐመረ ኖህ የሰንበት ትምህርት ቤት

---

## <u>የመካነ ሰላም መድኃኔዓለም አባት መዘምራን</u>

## <u>አመሠራረትና እንቅስቃሴ</u>

የዛሬ አምስት ዓመት በስድስት አባላት የተጀመረው የአባት መዘምራን ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አልፎ አልፎ በክብረ በዓላት ብቻ ወቅቱን

የሚመለከት መንፈሳዊ መዝሙር ሲአቀርብ እንደነበረ ይታወሳል። እንዲያም ይባል እንጂ እንደ ሐመረ ኖህና እንደ እናቶች መዘምራን ተደራጅቶ ተገቢውን አገልግሎት ሲሰጥ ቆይ ቷል ለማለት ፈጽሞ አያስደፍርም።

ዛሬ ግን የአባት መዘምራን በተጠናከረ መንፈሳዊ ይዘት ተደራጅቶ፤ መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ፤ የአገልግሎት አድማሱን በማስፋት የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ዘርግቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። ይኸው ሃያ ሰባት አባላትን የያዘው የአባት መዘምራን "የኦክላንድ መካነ ሰላም መድኃኔዓለም ተዋህዶ ካቴድራል የአባት መዘምራን" ተብሎ ተሰይሟል። በወር አንድ ጊዜም በካቴድራሉ ውስጥ እየተሰበሰበ ትምህርተ-ወንጌል፣ መንፈሳዊ መዝሙርና ያሬዳዊ ወረብ ያጠናል። ይህንንም ትምህርት የሚሰጡት የካቴድራሉ ዋና አስተዳዳሪ መልአከ ሰላም ቃለጽድቅ ሙሉጌታ ናቸው። ቀሲስ ወንድምነህ አስፋው ደግሞ የመዘምራኑ ተጠሪ ናቸው ።

የአባት መዘምራን በዚህ መልክ መደራጀት ለምንከተለው የክርስትና ሐይማኖት ጠንካራ ደጋፊ ከመሆኑም ባሻገር ተተኪው ትውልድም ይህንን ዓላማ ተከትሎ እንዲጓዝና በሃይማኖታዊ ትምህርትና ሥነ ምግባርም ታንጾ ለወደፊት መንፈሳዊ አገልግሎትን ለማገልገልና ለአገርም ጠቃሚ ዜጋ ለመሆን የተዘረጋውን የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮ በመከተል ነው።

በመሆኑም እኛ የአባት መዘምራን በአስፈላጊው መንገድ ሁሉ ከመካነ ሰላም ካቴድራል ጎን በመቆም የሚጠበቅብንን አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆናችንን በዚህ አጋጣሚ እንገልጻለን።

አባት መዘምራን

## መድኃኔዓለም የእናቶች ማህበር

እንኳን ለጌታችን ለመድኀኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ዓመታዊ በዓል በሰላም አደረሳችሁ/ አደረሰን።

የመካነ ሰላም መድኃኔዓለም የእናቶች ማሕበር የተመሠረተበትን ፲፩ኛ ዓመቱን ኦክላንድ መካነ ሰላም  መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ካቴድራል ጽዮን አዳራሽ

ውስጥ ጥር 23 ቀን 2001 ዓ/ም ብፁዕ አባታችን አቡነ መልከ ጼዴቅ ፣ ካህናት ፣ ዲያቆናት ፣ መዘምራንና ምዕመናን በተገኙበት በደመቀ ሁኔታ አክብሯል።

በዕለቱም ከማሕበሩ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት እናቶች መታሰቢያ እንዲሆን የጽዮን አዳራሽ ወጥ ቤትን በማሳደስ ለካቴድራሉ አበርክቷል። በወቅቱም የህሊና ጸሎት ተደርጎላቸዋል። ስለ ማሕበሩ ዓላማና ተግባር ቤተ ክርስቲያናችን የተመሠረተበትን 10ኛ ዓመት በተከበረ ጊዜ በወጣው መጽሔት ተገልጿል። ይሁን እንጂ የማሕበሩ አበላት ቁጥር በአሁኑ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ማሕበሩ እድገት እያሳየና እየጎለበተ መጥቷል።

ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን!

ከማሕበሩ ሥራ አመራር

# <u>ከወይብላ ማርያም ማህበርተኞች</u>

በመጀመሪያ እንኳን ለመድኃኒታችን ለመድኃኔዓለም ክብረ በዓል በሰላም አደረሳችሁ በማለት የወይብላ ማርያም ማሕበርተኞች ሰላምታችንን በአክብሮት እናቀርባለን። በመቀጠልም በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት በእናታችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የተደረገልንን ተአምር ለመግለጥ እንወዳለን! እነሆ የታመመው ከሞት ተነስቶልናል ፤ ብዙ ህሙማን ተፈውሰውልናል ክብር ምስጋና ይግባው ሥራ ያጣነው ሥራ ሰጥቶናል፤ የተለያዩ ችግርና ጭንቀቶች ተወግደው ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ጸሎቱ ተመልሶለታል። ማሕበርተኛ ያልሆኑ የእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነትዋን ዝናዋን በመስማት እንዲጸለይላቸው በጠየቁት መሠረት እንደ እምነታቸው ተመልሶላቸዋል ፤ ተአምር ተደርጎላቸዋል። ለእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ለቸሩ መድኃኔዓለም አባታዊ ፍቅር ያለ ምሥጋና ምንም የምንከፍለው ነገር የለም ክብር ምሥጋና ይግባው ለእኛ እንደደረሰልን በእናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ቸሩ መድኃኔዓለም እንዲደርስላችሁ ፤ ጸሎታችሁን እንዲመልስላችሁ ምኞታችን ነው።

የወይብላ ማርያም ማህበር

# <u>የበረከተ ወንጌል አምድ</u>

## <u>የዓለም ድኅነት</u>

የዓለም ድኅነት ባሰብንም በተናገርንም ጊዜ የዓለምንም ጥፋት ግድ እናስታውሳለን፣የዓለም ድኅነት ስንል ከምንድን ነው ዓለም የዳነው የሚለውን ጥያቄ በቀጥታ ያመጣብናልና።

ልዑል አምላክ የተከናወነ ዓለም ፈጥሮ ሁሉም መልካም እንደሆነ አይቶ በፍጥረቱም ሁሉ ደስ እንደተሰኘ የሥነ ፍጥረት ጊዜ ሁሉ ያስረዳናል። (ዘፍ ፩፥፲-፲፰)። እያንዳንዱን ፍጥረት አምላክ ፈጥሮ ሲፈጽም ይኸው መልካም እንደሆነ አየ እያለ ራሱ እግዚአብሔር እየተደነቀ እንደሠራው ያመለክታል። ከቶ እግዚአብሔር ጠልቶ የፈጠረው፤ ወይም ጎደሎ ፍጥረት አልፈጠረም፤ በሥነ ፍጥረቱም ላይ ጉድለት የነበረበት ፍጥረት ከቶ አልነበረም።

ለዚህ ዓለም ለተከናወነ ፍጥረት ኃላፊ ወይም ተመልካች አድርጎ የፈጠረው የሰው ልጅን ነው፤ እርሱም አዋቂ ሲሆን ከፍተኛም ፍጥረት ሲሆን ከሁሉም የተሻለ አእምሮ ያለው በመሆኑ ነው፤ ግን የሰይጣንን ምክር ሰምቶ አምላኩን አስቀየመ ሕጉን አፈረሰ ትእዛዙንም ጣሰ በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጣ ሰው በራሱ ላይ ቅጣትን አመጣ ። ከዚህ በኋላ ሰውና እግዚአብሔር ሰውና መላእክት ነፍስና ሥጋ ተጣሉ። ሰውም የዘለዓለም ቅጣትን ተቀባይ ሆነ፤ ረዳትም አጣ። ዓለም መልኩን ለወጠ የጥፋት ዓለም ተባለ፤ ከስሕተቱም ሊመለስ ሊድንም አልቻለም። ለብዙ ዘመንም የጠፋው ዓለም እየተባለ ቆየ በሞተ ሥጋ የሞተ ነፍስ ተጨመረበትና ስቃዩ መከራው በዛ።

ድኅነተ ዓለም ስንል እንግዲህ ከእንደዚ ካለው ጥፋት መከራ ዳነ፣ ነፃ ወጣ ማለትነው። እንዴት ነፃ ወጣ? ማንስ አወጣው ሰው በበደለ ጊዜ ከክቡር ቦታው በቅጣት መልክ በወጣ ጊዜ እግዚአብሔር — አምላክ የተስፋ ቃል ሰጥቶት ነበርና በተስፋው ቃል መሠረት ተቀምጦ ጠበቀ እንጂ በራሱ ጥረት ለመዳን የሰው ልጅ ያደረገው ነገር የለም፤ ብዙዎች ደጋግ አባቶች መሥዋዕት ሠውተዋል፤ ስብ አጢሰዋል፣ ደም አፍሰዋል፣ ይሁን እንጂ ሥራቸው ሁሉ አጸያፊ በመሆኑ እግዚአብሔር አልተቀበለውም።

እግዚአብሔር ከተቀየመ በኋላ ዕርቅ ሳይሆን የሚሠሩት ሁሉ የሚያስጠላ መሆኑን በነቢዩ ኢሳያስ አፍ እንዲህ ሲል ይናገራል። በሬ የሚያርድ እርሱ ሰው እንደገደለ ያለ ነው፣ በግም የሚሠዋ የውሻ አንገት እንደሚቆረጥ ነው፣ የእህልም ቁርባን የሚያቀርብ የእርያ ደም እነደማፍሰስ ነው ዕጣንም የሚያቀርብ ጣዖትን እንደሚያመሰግን ነው። እርሳቸው መንገዳቸውን መረጡ በክፋታቸውም ሰውነታቸው ደስ አላት ። (ኢሳ. ፷፮.፫ )።

እንደገናም ነቢዩ ሥራው ሁሉ የሚያጸይፍ እንደሆነ እንደደም ጨርቅ እንደሆነ እንዲህ ሲል ይናገራል። ሁላችንም እንደርኩስ ሆነ፣ ጽድቃችንም ሁሉ እንደመርገም ጨርቅ ሆነ፣ እኛም ሆላችን እንደቅጠል ረገፍን ኃጢአታችንም እንደነፋስ ወሰደን። (ኢሳ ፷፬፥፮) ።

በዚህ መልክ አስታራቂ አዳኝ ጠፍቶ ሰውም በራሱ ጥረት ሊድን የማይችል ሁኖ በግዞት ፣ በሞት ጥላ ሥር ይኖር ነበረ፣ ቅ.ጴጥሮስ የነፍሳትን ሁኔታ ሲገልጥ "ነፍሳቸው በእስራት ወደነበረችበት ሄዶ..." (፩ ጴጥ ፫፥፲፱ ) ሲል በግዞት በእስራት ሥቃይ ይኖሩ እንደነበር ያመለክታል። ቀጥሎም በራሳቸው ጥረት ሊድኑ አለመቻላቸውን ሲገልጥ "እንደ ጠፉ በጎች ሁናችሁ ነበር፣ ነገር ግን አሁን ወደ ነፍሳችሁ ጠባቂ ተመለሳችሁ" (፩ ጴጥ ፪፥፳፭)።

ነቢዩ ዳዊት የሰውን ልጅ ውድቀት በአንክሮ ተመልክቶ ምን ያህል ድቀት አግኝቶት እንደ ነበር ሲገልጥ " እግዚአብሔር ከሰማይ የሰውን ልጆች ተመለከተ የሚያስተውል እግዚአብሔርን የሚሻ ሰው እንዳለ ያዩ ዘንድ። ሁሉም አመጹ በአንድም ከነሱም በጎን ሠሪ የለም አንድስ እንኳን የለም" (መዝ.፲፬.፫-፬) ።

አሁን እንግዲህ በክርስቶስ የዓለም ድኅነት ሊሆን ነው፣ የዓለምን ጥፋት እንዴት እንደሆነ እንደተመለከትን ድኅነቱ ደግሞ ከእግዚአብሔር ቸርነት የተነሳ እንደሆነ እንመልከት።

1. እግዚአብሔር አዳምንም ዘሩንም ሁሉ ሲቀጣ ከተስፋ ውጭ አላደረገውም፣ የተስፋ ባለቤት እግዚአብሔር በተለያየ ጊዜ በተለያየ መልክ የተስፋ ቃል ሰጥቶናል ተስፋ ድምፅ አሰምቶናል። በመጀመሪያ ከገነት ሲያስወጣው "በአንችና በሲቲቱ

መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ በዘርሽና በዘርዋ መካከልም እርሱ ራስሽን ይቀጠቅጣል አንችም ሰኮናውን ትቀጠቅጫለሽ» ሲል ከሴት የሚወለደው ኢየሱስ የሰይጣንን ራስ እንደሚቀጠቅጥና ዲያብሎስ ድል ሲሆን የሰው ልጅ ሁሉ እንደሚድን የተስፋ ስንቅ ይዞ ወጥቷል። (ዘፍ.፫፥፲፭) ።

2. እግዚአብሔር ለአብርሃም የተስፋ ቃል ሲነግረው «በዘርህ የምድር አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ» ብሎታል (ዘፍ ፳፪፥፲፰ )። ይኸም ማለት ሕዝብም አሕዛብም አንድ ይሆናል የሁሉም የዳኑ ወገኖች ይባላል ሲል ትልቁን ተስፋ የክርስቶስን መምጣት አረጋገጠለት።
3. እንዲሁም ለይስሐቅና ለያዕቆብ የተስፋ ቃል አስተላልፎላቸዋል ይኸም ድኅነተ ዓለምን ያመለክታል (ዘፍ ፳፮፥፬. ፤ ፳፰፥፲፬)።
4. «ኢይጠፍዕ ምስፍና ወምልክና እምነ ዓባሉ ለይሁዳ እስከ መጽ ንጉሥ» ሲል ያናገረው የተስፋ ቃል ነው ( ዘፍ ፵፱፥፲ )። ይኸን የተስፋ ቃል የቀደሙ ረቢዎችና አስተማሪዎች መሢሕ እስኪመጣ እያሉ በተስፋ እንዲጠብቁ ያተጋቸው ነበር።
5. ነቢዩ ሙሴም «ነቢየ ያነሥእ ለክሙ እግዚአብሔር እምአኀዊክሙ ዘከማየ ወሎቱ ሳምዕዎ» ሲል ግልጥ የሆነ የተስፋ ቃል አስተላለፈላቸው (ዘዳ ፲፰፥፲፭)። ከሙሴ በኋላ ብዙዎች ነቢያት ተነስተዋል፣ ይሁን እንጅ የተስፋው ቃል ከነርሱ ለማንም እንዳልሆነ ግልጥ ነው፣ በቀጥታ የክርስቶስን መምጣት ድኅነተ ዓለም የሚጠብቅ የተስፋ ቃል ነበረ እንጅ።

ይኸ የተስፋ ቃል የተነገረው ለጌታችን ለኢየሱስ መምጣት መሆኑን ሲያመለክት እንደሙሴ ያለ ነቢይ ሌላ እንዳልተነሳ በዚሁ መጽሐፍ መስክሮ ጽፎ ይገኛል ራሱ ክርስቶስም ሲያስተምር በሙሴ የምታምኑ ከሆናችሁ በኔም ባመናችሁ ነበር፣ ሙሴ ስለኔ መስክሮ ጽፏልና ሲል ተናግሯል (ዮሐ ፭፥፵፮)።

ጊዜው ሲደርስ የተስፋው ዘመን ሲፈጸም የዓለሙን በደል የሚያሥተሥርይ ኢየሱስ ሰው ሆነ፥ ሥጋንም ለበሰ/ የሰውም ድኅነት በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ። መዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ስለሆነ ገና ሲወለድ አስቀድሞ መልአክ እንደሰየመው ኢየሱስ ተባለ (ማቴ፩፥፳፩)።

ወንጌላዊው ሉቃስ መዳን በማንም በምንም አለመሆኑን ፣ እነድንበት ዘንድ በተሰጠን ስም ከሰማይ በታች ምንም የለምና በኢየሱስ ሆነ (የሐ.ሥራ ፬፥፲፪) ። ድኅነተ ዓለም ከጥንቱ በእግዚአብሔር ቃል በወልድ ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ነቢዩ ኢሳይያስ «ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና» (ኢሳ ፱፥፮)። ለኛ የተሰጠ፣ ለድኅነታችን የቆመ መሆኑን የሚያመለክት ሕፃን ተወልዶልናልና አለ እንጅ ዝም ብሎ ሕፃን ተወልዷል አላለም። ክርስቶስ የሁላችን ገንዘብ፣ ለሁላችን ለየአንዳንዳችን የተሰጠ መድኃኒት ነው። አሁንም ድኅነት በማንም አይሆንም አይደረግም ካለፈው ጥፋት ዓለም የዳነው በኢየሱስ ብቻ ነው፣ ዛሬም አዳኛችን ኢየሱስ ነው፣ ድኅነት በማንም የለም ሊሆንም አይችልም።

ለዓለም አንድ ነገር ባላደረጉ ሩቅ ብእሲዎች ዓለም ይታመናል፣ ለምሳሌ ከክርስቲያን እምነት ውጭ በሆኑ ዓለም ሲማረክ ሲያመልክባቸውም ይታያል፣ የዓለሙ መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ተረስቶ ወይም ችላ ተብሎ ይገኛል።


እነሆ አሁንም እንደ አዲስ የምሥራች አድርጌ የምናገረው «ወንድ ልጅ ተወልዶልናልና» ማለት ወንድ ልጅ ተሰጥቶናልና ከጥቃት የሚያድን ከጠላት የሚቤዠን! በእርሱ እንመን፣ እርሱን እናምልክ፣ እርሱ ቤዛችን ነው! እርሱ መድኃኒታችን ነው!

ከብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ

## ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ

«ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ ያለእርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና» (ዕብ. 12፥14)

በዚህ ባለንበት ዘመን አንድ በሽተኛ ዶክተሩን ለማየት ወደ ሆስፒታል ሲሄድ መፈጸም ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። በሽተኛው በመጀመሪያ ዶክተሩን ከማየቱ በፊት በነርስዋ በኩል ደሙን መለካት፣ ክብደቱን መመዘን፤ የትኩሳት መጠኑን መመርመር፤ የማንኛውም መድኃኒት አለርጂክ መሆኑንና አለመሆኑን በሚገባ ማስረዳት ይጠበቅበታል። እንዲሁም ቀደም ሲል የተለያየ ህክምና ማድረጉንና አለማድረጉንም ጭምር በማስረዳት በነርስዋ በኩል ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ ዶክተሩን ያያል የተሟላ እንፎርሜሽንም ይዞ ይቀርባል። እንደዚሁ ቅዱስ ጌታን ለማየት መቀደስ የግድ አስፈላጊ መሆኑን እንዲህ ሲል ያረጋግጥልናል፣- «ትቀደሱ ዘንድ ፈልጉ ያለእርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና»።


Messob
Ethiopian Restaurant
"Messob has Charmed Piedmont Avenue...In favor of the deeply spiced stews"
J.Kauffman East Bay Express 06'
Outdoor Patio
Open Daily from 11am-10pm
4301 Piedmont Ave. Oakland
510.428.1122


የተሟላ ምግብ ቤት
ኢትዮጵያዊ መስተንግዶ
ልዩ ሙያና ባልትና
Design - Ethio Graphics 408.489.0851
የት ነው ይሄ ሁሉ?
Zeni
Ethiopian Restaurant & Bar
ዘኒ
የባህል ምግብ ቤት
1320 Saratoga Ave. San Jose, Ca 95129
408.615.8282





የቀሲስ ወንድምነህ የቅስና ሹመት

የእናት መዘምራን



የመካነ ሰላም መድኃኔዓለም የሐመረ ኖህ የሰንበት ት/ቤት የመድኃኔዓለምን በዓል ሲያከብሩ

**መቀደስ ማለት ምን ማለት ነው? ሰው ራሱን በምን ይቀድሳል? በዚች ርኩሰት በሚታወጅባትና ጥፋት በነገሠባት ዓለም ቅድስናን ማግኘት እንዴት ይቻላል? ማንም ሰው ራስን ስለመቀደስ ቢጠይቁት እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንደሚያነሳ ጥርጥር የለውም። በመሆኑም የእግዚአብሔር ቃል በሚያስተምረን መሠረት እንደሚከተለው እንመልከት፣-**

**«ቅድስና» የሚለው ቃል ቀደሰ ከሚለው ግሥ የመጣ ቃል ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምሮ በሁለት መንገድ ይፈታል።**

1. **ቅዱስ ማለት ልዩ ከሁሉም ነገር የተለየ ሲሆን**
2. **ቅዱስ ማለት ንጹሕ ፣ ክቡር ማለት ነው**

**እግዚአብሔር ይህንን ቃሉን ያወጀው የቅድስና ምንጭ ከሆነው ከማንነቱ በመጀመር ነው። ለሙሴ ሲናገር ፥ «እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ» ነው ያለው!** {**ዘሌ**. 19፣2 ፤ 1. **ጴጥ**. 1፣15} **እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ የሚቀድስ ቅዱስ አምላክ ነውና ወደእርሱ ለመቅረብና የምህረት ፊቱን ለማየት መቀደስ ያስፈልጋል።**

- **<u>እግዚአብሔር ቅዱስ ነው</u>**

1. **በባህርይው ቅዱስ (ልዩ) (ከአማልክት ሁሉ የተለየ ነው)**
   **«አቤቱ ፥ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው? በምስጋና የተፈራህ ፥ ድንቅንም የምታደርግ»** (**ዘጸ**.15፣11፣**ኢሳ**.40፣25)

2. **በምስጋናው ቅዱስ (ልዩ) ነው** (**ኢሳ**. 6፥3 ፤ **ራዕ**. 4፥8)
   **«አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው ፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል ፤ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም»**

3. **ስሙ ቅዱስ ነው**
   **«ለዘላለም የሚኖር ስሙም ቅዱስ የሆነ ፥ ከፍ ያለው ልዑል እንዲህ ይላል። የተዋረዱትን ሰዎች መንፈስ ሕያው አደርግ ዘንድ ፥ የተቀጠቀጠውንም ልብ ሕያው**

አደርግ ዘንድ ፥ የተቀጠቀጠና የተዋረደ መንፈስ ካለው ጋር በከፍታና በተቀደሰ ስፍራ እቀመጣለሁ» (ኢሳ. 57፥15 ፣ ሕዝ. 36፥20)

«ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና ፤ ስሙም ቅዱስ ነው» (ሉቃ 1፥49)

ቅዱስ እግዚአብሔር ማንነቱን የሚገልጸውን ቅድስና ካወጀ በኋላ ልጆቹን እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ይላል። የቅዱስ እግዚአብሔር ልጆች ቅዱሳን ናቸውና (ዘሌ. 19፣2 ፤ 1. ጴጥ. 1፥15)። ይህም ማለት ልጆቹ ከርኩሰት ዓለም ተለይተው ፤ ክፉንና የጨለማውን ሥራ አስወግደው የቅዱስ እግዚአብሔርን ጠባይ (ባህርይ) እንዲመስሉ ስለሚፈልግ ነው። በዚህ ዓለም የልጆቻቸው አስተዳደግ የሚገዳቸው ወላጆች ልጆቻቸው ቴሌቭዢን እንዲያዩ የሚፈቅዱላቸውና የማይፈቅዱላቸው ቻናል አለ። ምክንያቱም ለአእምሮአቸው የማይመጥን ብዙ ርኩሰትና ክፋት ሁሉ መልካም በሆነው ነገር ውስጥ ስለሚተላለፍ ነው። እንደዚሁ ለልጆቹ የሚጠነቀቅ እግዚአብሔር አምላክ እርሱ ለቅድስና የጠራቸው ልጆቹ ቅዱስ ህዝብ፤ የርስቱ መንግሥት ስለሆኑ ከዓለም ርኩሰት እንዲለዩ ይመክራል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ቅዱሱ እግዚአብሔር የሚገለገልባቸው ነገሮች ሁሉ ቅዱሳን እንደ ሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ያውጃል።

1. እግዚአብሔር የሚመሰገንባቸው ቀኖች ቅዱሳን (የተለዩ) ናቸው
   {ለምሳሌ፥ አይሁድ የሚያከብሩአቸው ሰንበትና የዓመት በዓላት}።
   «እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም ፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ አርፎአልና» (ዘፍ. 2፥3)

2. እግዚአብሔር የሚመሰገንበት ቦታ ቅዱስ ነው። (ልዩ)
   «ወደዚህ አትቅረብ ፤ አንተ የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው» (ዘጸ. 3፥5)

3. ለእግዚአብሔር መሥዋዕት የሚቀርቡ እንስሳት ቅዱሳን ናቸው
   «በእስራኤል ልጆች ዘንድ ከሰውም ከእንስሳም ማሕፀንን የሚከፈት በኵር ሁሉ ለእኔ

ቀድስልኝ ፤ የእኔ ነው» (ዘጸ. 13፥2)

4. ብርና ወርቁ ሳይቀር በአጠቃላይ የእርሱ የሆነው ነገር ሁሉ ቅዱስ እንደሆነ ያውጃልናል «ነገር ግን ብርና ወርቅ ሁሉ የናስና የብረትም ዕቃ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይሁን ፤ ወደ እግዚአብሔርም ግምጃ ቤት ይግባ»(ኢ.ያ. 6፥19)

❖ <u>ሁሉን የቀደሰ ቅዱሰ ቅዱሳን</u>

ነገር ግን ከኃጢአት የተነሳ በብሉይ ኪዳን የታወጀው የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ዘንድ ተፈጻሚነት አላገኘም። የሥጋ ድካም ጽድቅን ሊያመጣ አልቻለም። ኢሳይያስ በትንቢቱ እንደተናገረ የኦሪት የጽድቅ ሥራ ሁሉ መርገም ሆነ። {ኢሳ. 64፥5-7} ከሰው የተነሳ ምድርም ረከሰች። ከእንስሳትም የሚበሉና የማይበሉ ተብሎ ህግ ተደነገገ ፤ ስለዚህ የቅድስና ስሜት የራቀው ፤ ኃጢአት አንገቱን ያስደፋው ፤ በሥጋው ርደተ መቃብር በነፍሱም የዘለዓለም ሞት የተፈረደበት ሆነ። በመሆኑም የአብርሐም እምነት ቅድስናን አላመጣም። የዳዊት ዝማሬ ፤ የአበው መሥዋዕትም ድኅነት አላመጣም። ስለዚህ <u>ሰው እግዚአብሔርን በጠባዩ (በቅድስናው ባህርይ) መምሰል ስላልቻለ እግዚአብሔር ሰው ሆነ</u>። ፍጹም ሰው የሆነውን ልጁን ወልደ እግዚአብሔር ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ወደ አለም ላከ። እርሱ እኛን ሆኖ ተገለጠ፤ እኛን መሰለ፤በሥጋና በደም ተካፈለ። ቃሉ እንደሚለው፥ «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር ይኸውም ዲያብሎስ ነው በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። የአብርሐምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም» (ዕብ. 2፥15)

1. <u>እርሱ ስለቅድስናችን ጸለየ</u>፤

«በእውነትህ ቃል ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነውና። ወደዓለም እንደላከኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤ እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ» (ዮሐ. 17፥16)

2. <u>እርሱ ስለ ሰላማችን የዘለዓለም መሥዋዕት ሆነ፤</u>

ወደ ቅድስና ሥፍራችን ሊመልሰን ወደ ቅዱስ አባቱም ሊያቀርበን በመሐከል የነበረውን ግርግዳ በሥጋው አፈረሰ። እንደዚህ ተብሎ እንደተጻፈ፥

«እርሱ ሰላማችን ነውና ፤ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ» (ኤፌ. 2፥15)

3. **እርሱ ለቅድስና ጠርቶናልና።**

«ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር ለቅድስና ተጠርተናል እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ አይደለም መንፈስ ቅዱስን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ» (1. ተሰ. 4፥8)።

ዛሬ ከዓለም ርኩሰት ለማምለጥ ብቸኛው መንገድ የነፍሳችን እረፍትና እርካታ የሆነው የእግዚአብሔር ቃልና የዓለምን ማአበልና ወጀብ የምንሻገርበት መርከባችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነች። ዓለም ወዴት እያመራ እንደሆነ እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ምን እያደረገ እንደሆነ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ አማኝ ሁሉ በትክክል ሊናገረው ሊረዳው የሚችለው ሀቅ ነው። ስለዚህ በኑሮአችን ቅዱሳን እንዲንሆን ተጠርተናል። «የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ»(1. ጴጥ. 1፥15)

በዘመናችን ብዙዎች ክርስቲያኖች ለቅድስና ያላቸው አመለካከት በጣም ከእግዚአብሔር ቃል የራቀ ነው። በመሆኑም ቅድስናን በሦስት መንገድ ይሸሹታል ወይም ራሳቸውን ከቅድስና ያርቃሉ።

1. ቅድስናን ለተወሰኑ ቅዱሳን ብቻ በመመደብ ።
2. ቅድስናን በእድሜ መከለል
3. ቅድስናን በቦታ በመመደብ የተሳሳተ አመለካከት ይከተላሉ

እግዚአብሔር ግን በስሙ የተጠሩትንና ዳግም ከእርሱ የተወለዱትን ቅዱሳን ብሎ ይጠራቸዋል።

«በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ ፥ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን» (ሮሜ 1፥7)።

«በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት ፥ የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት» (1. ቆሮ. 1፥2)

ስለሆነም እለት እለት ቅድስናን በመሻት ፤ የቅድስናንም ኑሮ በመኖር ፤ እርሱን ጌታን በቅድስናው ዙፋን ማየት እንድንችል ፤ የቅድስና ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ጋር መመሳለስ ይገባናል።

- ❖ **ማጠቃለያ**

**<u>የቅድስና ፍሬዎች</u>**

የቅድስና ሕይወትን ለመኖር፤ የቅድስና ፍሬን ለማፍራት በእግዚአብሔር ቃል መኖርና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መመላለስ ሲሆን እርሱም በሚከተሉት መንገዶች ይገለጣል።

1. የእግዚአብሔርን ቃል የእለት ከእለት መመሪያችን ማድረግ (ቈላ. 3፥16)
2. በቅዱስ ቁርባን ከጌታ ጋር ባለን ሕብረት መመላለስ (ዮሐ. 6፥56)
3. በንሥሐ የእለት እለት ሕይወታችንን ማደስ አለመዘንጋት (2.ቆሮ. 4፥16)
4. ዓለምን አለመምሰል ነገር ግን በልብ መታደስ መለወጥ (ሮሜ. 12፥2)

ምስጋና ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን ዛሬም ለዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን!

መልአከ ሰላም አባ ቃለጽድቅ ሙሉጌታ

# <u>አገልግሎትና አገልጋይ</u>

1ኛ <u>የአገልግሎት ምንነት</u>

በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሰዎች እግዚአብሔር ብዙ ስጦታዎችን ይሰጣል 1ኛ ቆሮ.12፥13-14 ኤፌ 4 ፤ ሮሜ 12። በነዚህ ስጦታዎች ተጠቅሞ የሰጠንን ጌታ ማምለክና ማገልገል

የክርስትያናዊ ውዴታ ግዴታ ነው። የአገልግሎት መሰረቱ በክርስቶስ ደም ነጽቶ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተቀድሶና ተሞልቶ ጤናማውን የክርስትና ሕይወት መኖር ነው። አገልግሎት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ታማኝነት ጭምር ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ጉዳይ ከልባችን ጋር መሆን አለበት ማለት ነው፤ የሕይወት መውጫ ከልባችን ነውና አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና። ምሳ 4፥3

2ኛ <u>ከአገልግሎት በፊት ማወቅ ያለብን ነገሮች</u>

ሀ - <u>የጠራንን ጌታ ማወቅ</u> በተፈጥሮ ጠባዩንና ማንነቱን የማንረዳውን ሰው እንኳ ማገልገል አስቸጋሪ ነው። ስለዚህ አገልጋዩ የአምላኩን ማንነት ማወቅ አለበት። ቅድስናውን፤ ችሎታውን ፤ ሀይሉን ፤ ፈጣሪነቱን ፤ አዳኝነቱን ፤ አባትነቱን ፤ ፍቅሩን ፤ መሀሪነቱን ፤ ፈራጅነቱን። ስለዚህ ከአገልግሎት በፊት የሚቀድመው ነገር እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ መረዳትና በኑሮም በአገልግሎት ሁሉ ስልጣንን ለእርሱ መስጠት።

ለ. <u>እኛነታችንን ማወቅ</u> እግዚአብሔር የራሱ እንድንሆን ሲጠራን እኛም ግብዣውን ተቀብለን ህይወታችንን ለአምላካችን ስንሰጥ የእግዚአብሔር ሆነናል ማለት ነው።

«በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በስጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ ይለናል» 1ኛ ቆሮ 6፥20

ማንነቱን የማያውቅ አማኝ ላገልግሎት አይበቃም። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ እኖራለሁ እርሱም ብዙ ፍሬ ያፈራል። (ዮሐ 15፥5)

ሐ- <u>ኃላፊነትን ማወቅ</u> ቈላ. 4፣7 ፤ 3፥2

መ- <u>አማኝ የሆነ ሁሉ አገልጋይ እንደሆነ ማወቅ</u> 1ኛ ቆሮ12፥4-6

ሠ- <u>የአገልግሎት ክቡርነት ማወቅ</u> 2ኛ ቆሮ 4፥7

3ኛ <u>የአገልግሎት ጥሪ</u>

ለአገልግሎት በመጀመሪያ መጠራት ያስፈልጋል። ከቀደሙ አባቶች ጀምሮ ማለትም ከብሉይ ኪዳን እስከ አዲስ ኪዳን ያሉትን አባቶች እግዚአብሔር ለአገልግሎት በመጀመሪያ ጥሪ እንዳደረገላቸው ነው የምናየው።

- ሙሴን «ህዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ታወጣ ዘንድ እልክሀለው»ዘፀ 3፥10
- ኤርሚያስን «የማዝህን ሁሉ ትናገራለህ ብላቴና ነኝ አትበል» 1፥4-7
- ኢሳይያስን «ሂደህ ይሄን ህዝብ እንዲህ በል»
- ለደቀመዛሙርቱ «ከኋላዬ ተከተለኝ» 1፥9
- ዻውሎስን «ስሜን በአህዛብና በነገስታት ፊት የሚሸከም» ሐዋ 9፥15

## ሁለት አይነት አገልጋዮች አሉ

| በሥጋ የተጠሩ | በእግዚአብሔር የተጠሩ |
|---|---|
| * በራሳቸው ይታመናሉ | * በእግዚአብሔር ይታመናሉ |
| * ምኞታቸውን ለመፈጸም ይተጋሉ | * የመጣውን ጥሪ በአክብሮት ይቀበላሉ |
| * በኩራትና በትእቢት ያገለግላሉ | * በትህትና ያገለግላሉ |
| * ቃሉን ለስጋ እንዲመች አድርገው ያጣምማሉ 2ኛ ቆሮ 17 | * በቃሉ ይጠራሉ በትህትና ያገለግላሉ መዝ 118፥105 |
| * ማዘዝን እንጂ መታዘዝን አያውቁም | * ይታዘዛሉ |
| * መመስገን ይፈልጋሉ | * ምስጋና ለሚገባው ምስጋና ይሰጣሉ ሮሜ13፥7 |
| * ያደረጉትን ይቆጥራሉ ሉቃስ 18፥11 | * ያደረጉትን አይናገሩም ዋጋቸው በሰማይ ነውና ሉቃስ 17፥10 |
| * መናገር እንጂ ሌላውን አያዳምጡም | * ሌላውን ያዳምጣሉ |
| * ሀሳባቸው ምድራዊ ነው | * ሀገራቸው በሰማይ ነው |
| * ማጉረምረም ያበዛሉ ወዘተ… | * ምስጋና ያበዛሉ ወዘተ… |

እንግዲህ በዘመናችን እንደምናየው በሥጋ የተጠሩት አገልጋዮች ጊዜያዊ በሆነ ጥቅምና ክብር የወንጌልን እውነት ደብቀው ህዝቡን ሲያሳስቱት በእግዚአብሔር የተጠሩት ይህ ዓለም አልሰማቸው እንኳን ሲል ክብር ለሚገባው ክብር እየሰጡ ለምድራዊ ምኞት ሳይበገሩ በእውነት እየተጋደሉ ይገኛሉ። በዚህ ዘመን ላለ ክርስቲያን ይህንን ለመለየት አይቸገርም ግልጽ ነውና።


ETHIOPIA RESTAURANT
ኢትዮጵያ ምግብ ቤት
Catering .
Banquets.
Weddings.
The Best Ethiopian Food!
Authentic Ethiopian Ambiance
Meskerem Tsegaye
መስከረም ፀጋዬ
2955 Telegraph Ave
Berkeley, CA. 94705
Tel: (510) 843-1992
WWW.ETHOPIARESTURANT.COM


ABYSSINIA TRADING, LLC
ምርጥ የኢትዮጵያ ምርቶች
ቀጥታ ከኢትዮጵያ
አስመጪና አከፋፋይ
WHOLE SALE
DISTRIBUTOR
ETHIOPIAN PRODUCT
Brown and Mixed Teff flour
Home-made hot and spiced pepper
Ashiaro and much more
ABYSSINIA TRADING LLC proudly presents
the best products from the heartland of Ethiopia.
በኛ ጤፍ እንጀራ ለመጋገር
የግዴታ ሰልፍራይስ ወይም
ሌላ ነገር መደባለቅ አያስፈልግም
You can find our products at any
Ethiopian retail stores and
Middle Eastern Foods, @
Washington St, S. Clara
For questions on how to make
Injera and direct orders please call at:
(408) 396-8952
(408) 891-3065
For any other questions :
3068 Kenneth Street
Santa Clara, CA 95054
Tel: (408) 727-9300
Fax:(408) 727-9301


ALBO
Travel
Agency
We specilze in last minute domestic and
international fares!
አልቦ የጉዞ ወኪል
LOWEAT FAREES TO
ADDIS , ABABA ,ASMARA, EUROP, ASIA & ISLANDS
510 428 2526
510 222 7270


OVER 15 YEARS EXPERIENCE
ALL NEW
DIGITAL EQUIPMENT
Sunset Video Production
Tel: (510) 915-2157
zee@sunsetvideoproduction.com
www.sunsetvideoproduction.com


እንኳን ለመድኃኔዓለም
በአል አደረሳችሁ
የእናት ጠጅ
"TEJ" is a unique drink of Ethiopian tradition.
Produced from Honey and a unique form of hops
called "Ghesho". It is a Natural Wine
without sulfites and No Preservatives.
Enjoy it's fresh Honey taste.
"You Will Love It!!"
+ = mmmmgood!!!
Enat Winery
910-81st Avenue # 18
Oakland, CA 94621
Office: (510) 632-6629
Fax : (510) 632-1651
Email: hhou723489@aol.com

## 4ኛ የአገልግሎት ዝግጅት

ለአገልግሎት እንደተጠራን ዘው ብለን መግባት የለብንም ዝግጅት ያስፈልጋል።

- ኖህ ለ150 ቀናት የሰው ዘር ለማስቀረት 120 አመት ተዘጋጅቷል
- ኢያሱ ቢያንስ 40 ዓመታት የሙሴ አገልጋይ ሆኖ ተዘጋጅቷል
- ሳሙኤል ከሕፃንነቱ ጀምሮ መዘጋጀት የጀመረው
- ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ለ14 ዓመታት ያህል በእስር ቤት ሲዘጋጅ ነው የኖረው
- ዳዊት ንግስና የተቀበለው ገና በልጅነቱ ነበር የነገሰው ግን በ30 ዓመቱ ነው
- እየሱስ ክርስቶስ ለ3ዓመት አገልግሎት 30ዓመት ነበር የተዘጋጀው
- ሐዋርያት ከመላካቸው በፊት በኢየሱስ እግር ስር 3 ዓመታት ተዘጋጅቷል

በአጠቃላይ ዝግጅት ሲባል የመንፈስ ዝግጅት፣ የአእምሮ ዝግጅት፣ የስጋ ዝግጅት ያስፈልጋል

## 5ኛ ከአገልጋይ የሚጠበቁ ነገሮች (ራእይ)

ሀ - መገለጥና ማስተዋል ይህ ከሥጋና ከደም ወይም ከትምህርት ብዛት የማይገኝ ከእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ የሚሰጥ ነገር ነው። ጌታ ስለመረጣችው አገልጋዮች እንዲህ አለ «........ከጥበበኛችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕጻናት ስለገለጥክላቸው አመስግንሀለሁ......» ማቴ 11፥25 ተስ 1፥5 ሰሎሞንም እንዲህ አለ «አሁንም በዚህ ህዝብ ፊት እወጣና እገባ ዘንድ ጥበብንና እውቀትን ስጠኝ» 2ዜና 1፥10

ለ - ትሑት ልብ አገልግሎት ጤናማ የሚሆነው አገልጋዩ ትሑት ሩህሩህና በፍቅር የተሞላ ልብ ሲኖረው ነው። ጌታ ስለራሱ ሲናገር «እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝ» ብሎ እኛም ከእኔ ተማሩ ባለው መሰረት ከእርሱ መማር አለብን። ማቴ 11፥29 ፍቅር የሌለው አገልግሎት ትርጉም የሌለው ቃጭል ነው 1ኛቆሮ 13፥1-2

ሐ - የአገልግሎት መንፈስ አገልጋይ ቆሞ መስበክ፣ መዘመር ... ብቻ ሳይሆን ዝቅ ብሎ ተንበርክኮ እግር ማጠብም ነው። ልንገለገል ሳይሆን ልናገለግል ጌታ ጠርቶናልና ማር 10፥43

መ - <u>ሙያ ወይም ችሎታ</u> መማር ፣ ማንበብ ፤ ከላይ ካሉት ህይወትም ሆነ ልምድ መቅሰም ያስፈልጋል።

ሰ - <u>በቃሉ ራስን ማሳደግ(ኢያሱ 1፥2-9)</u> በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሰረተ አገልጋይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማገልገል አይችልም

ረ - <u>የፀሎት ሕይውት</u>

6ኛ <u>የአገልገሎት እንቅፋቶች</u>

«አንተ ግን ከዚህ ሁሉ ሽሽ ፅድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፣ ፍቅርንም፣ መጽናትንም ፣ ተከታተል» 1ኛ ጢሞ 6፥11። ማንኛውም አገልገይ እግዚአብሔርን ከሚያስበልጡበት እንቅፋቶች ራሱን ማሸሸ አለበት ማለትም ከገንዘብ ፍቅር ፣ ጤናማ ካልሆነ የጾታ ግንኙነት ፣ ሚዛናዊ ያልሆነ የስልጣን አጠቃቀም ፣ ለዝናና ለተወዳጅነት ብሎ ማገልገል ፣ ወዘተ...2ጢሞ 2፥2, ዘፍ 39፥1, ማቴ 6፥2, ማቴ 6፥1

7ኛ <u>የአገልገሎት ጥቅሞች</u>

እግዚአብሔርን በቅን እና በቃሉ መሠረት ብናገለግለው ቡዙ ሽልማቶች አዘጋጅቶልናል።

ሀ - **የጽድቅ አክሊል መቀበል** «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫዬን ጨርሻለሁ ሃይማኖቴን ጠብቄአለሁ፤ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል......ደግሞም መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» 2ጢሞ 4፥2-8

ለ - **እንደ ሰማይ ከዋክብት ማብራት** «ጥበበኛች እንደ ሰማይ ጸዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።ይላሉ

ሐ - **የዘላለም ሕይወት** «እኔ የዘላለም ሕይወት እሰጣችኋለው ለዘላለም አይጠፋም ከእጄም ማንም አይነጥቃችሁም» ዮሐ 10፥28 ማቴ 23፥34 1ጴጥ 2፥9

እንግዲህ የአገልግሎትን ምንነትን ተረድተን ፣ የጠራንን ጌታ አክብረን ፣ ማንኛውም ክርስቲያን በውሰጡ ጌታ ያስቀመጠውን የአገልግሎት ስጦታ ፈልጎ አግኝቶ የዚህ ዓለም የውሸት ሕይወት ሳያታልለን በሚገባ መንፈሳዊ ግዴታችንን ተወጥተን ማለፍ ይገባናል። ለዚህ ሁሉ የሁሉ ባለቤት የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ይርዳን።

አሜን!!!

ከዘማሪ ዲ. እንዳልካቸው

## The Biblical Ethiopia

**"Ethiopia stretching out her hands unto God. Psalm 68:32"**

The name Ethiopia has been mentioned more than 45 times in the Bible. Some of the so called Bible scholars have said **"The name of the modern country did not acquire the name Ethiopia until the 20th century. It had been called Abyssinia. But this misleads people, including the Ethiopians themselves to connect references to Ethiopia in the Septuagint and in the New Testament to their country."** In some cases like the American Bible Society went too far and replace the name Ethiopia with Sudan in their past version. Although what they have stated and done is very offensive to millions Ethiopians, I am writing this note in what appeared to be a fit of pique but to confute the deliberate error made by them. It is possible to debate in great depth with regard to this issue as the Ethiopian history is so immense and lots of supporting documents are available. Yet it is beyond the scope of this article to provide comprehensive review of the whole field. However, I just briefly outlined below when and where the name Ethiopia originated and who is the Biblical Ethiopia?

**Ethiopian source**

The term Ethiopia used in the past to describe the country south of Egypt that stretching to India. However, throughout the centuries that prodigious country dwindled to its present shape for many reasons. I leave aside why the Ethiopian empire has lost all its territories, as it is not the main objective of this article but to show the term Ethiopia did not crop up in the 20th century but has been used for centuries in our country in all aspects of life.

First, according to the Ethiopian traditions, the name Ethiopia first was used after the Ethiopian King Aethiops I who reigned around 1860 BC and the natives have been called

Ethiopians after him ever since. Therefore, the name Ethiopia originated 2000 years before Christ, even before the Greeks used it to describe the people below south of Egypt.

Second, since Judaism was introduced in Ethiopia around 950 BC Ethiopians annually used to go to Jerusalem to worship the God of Israel. This is backed by St. John Chrysostom who lived in the fourth century mentioned the presence of Ethiopians in the Holy City on the day of Pentecost. We know that Ethiopians have been worshipping the God of Israel ever since. The Ethiopians at the time and even now have been making pilgrimages to the Holy Land.

Even after the conversion from Judaism to Christianity, the Ethiopians have been paying visits to the Holy Land and established monasteries in most holy places wherever our Lord Jesus Christ taught and performed great deeds. And these holy places are still in our possession. Their presence, way of life and places possessed described by many European pilgrims throughout generations who also said "the Ethiopians are the most pious of all monks" in Jerusalem. One of the earliest European accounts about the presence of Ethiopian Christians in the Holy Land was the Latin Church father St. Jerome who lived in Bethlehem around 386 AD.

Third, the famous Ethiopian Church music composer St. Yared who lived in the sixth century has used the term Ethiopia in his Hymns. **«እግዚኦ ኩነኔከ ሀቦ ለንጉሥ፤ ወይምላእ ስብሐቲሁ ኩሎ ምድረ ለይኩን ለይኩን። ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሁ።ስብሐት ለአብ ለወልድ ለመን ፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም።»**

Fourth, those resplendent Ethiopian monarchs for instance Emperor Amde Tsion and Emperor Zera Yacoub who lived in the 14th century mentioned in their letters "Emperors of Ethiopia..." These letters are currently archived at the Vatican Library.

Fifth, the famous Emperor Lebene Dingel who lived in the 16th century composed a prayer which later on added to the early Morning Prayer "Seatat" or the Horologium mentioned the term Ethiopia too. **«በእንተ ፍቅረ አብ ፣ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ ኬንያ፣ እስእለኪ ማርያም በሃሌ ሉያ፣ ሀዘና ስምዒ ወብካያ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ»**

**Other sources**

The relationship between Ethiopia and Israel goes back to Antiquities. King David had the desire to build the Temple of God but he never succeeded. However, his son King Solomon, who reigned some 40 years (970- 930 BC) decided to build the Temple of

Yahweh; and in order to provide the materials for the building he sent out his ships to various countries. One of these places was the land of Ophir/Punt which is situated on the west coast of the Red Sea. Many Ethiopist reckon that the name Afar might be derived from the name Ophir which is situated in the northeast of Ethiopia. The main reason for King Solomon sending his ships to this part of the world was, because of the high commercial and maritime activity on the coast of the Red Sea. It is well know that the Egyptian Pharoses have had commercial link with the land of Punt/Ophir since 3000 BC. The main imports were gold, platinum, Myrrh, eye cosmetic and other ingredients. There are lots of reasons to support this land of Punt is situated within the present Ethiopian state. In recent times Kings Solomon's gold mines have been discovered in the southern part of Ethiopia. So it is more unlikely to connect Zimbabwe as King Solomon's mines. One of the good reason for importing materials from Ethiopia could be the quality as it is mentioned in Job 28:19 "The topaz of Ethiopia shall not equal it."

The prophet Isaiah who lived in the 8th century BC tells us "Woe to the land shadowing wings, which is beyond the rivers of Ethiopia: that sends ambassador by the sea, in papyrus skiffs over the waters. Is.18: 1" First, this verse clearly indicates that the country must be on the West coast of the Red Sea which is Ethiopia as the neighboring kingdom at Napata was far from the Red Sea Coast and where the Niles join. Secondly, the kingdom at Napata or Meroe at the time tends to use the land route via Egypt. Thirdly, it is still very much in use of papyrus boats in Lake Tana, northwest of Ethiopia. Fourthly, on this chapter verse 3 it says, "…the signal being hoisted on the mountains, look!" If we take this verse, Ethiopia is the only mountainous region compare to the Sudan or Egypt. Therefore, it is the present Ethiopia which is mentioned in Isaiah.

The prophet Zephaniah (640-609 BC) prophesized that " From beyond the rivers of Ethiopia my suppliants, even the daughter of my dispersed, shall bring mine offerings Zep.3: 10." This prophesy clearly tell us that the long term commercial links between Israel and Ethiopia and above all the dispersed children of Israel would go back to the land of their ancestors. This exodus is a very recent event that thousands of Ethiopian Jews (the Falasha) immigrated to Israel.

Jeremiah (605 BC) mention "Now when Ebde-Melech the Ethiopian, one of the eunuchs which was in the kings house, heard that they had put Jeremiah in the

dungeon…Jer.38: 7.” It has been a custom to use eunuchs in the house of the Ethiopian Royal household till the time of the last Emperor Haile Selassie. So we can see some kind of connection between the Royal household of Ethiopia and Israel. For instance It has been said by the classical writes or other travelers, the Ethiopians are known for being very amenable to reason and justice, a good natured, kind and so inclined to forgiveness that they readily pardon any injuries. The benevolent Ebde-Melech is one typical example.

Jeremiah also mention in chapter 46: 9 “Come up, ye horses; and rage, ye chariots; and let the mighty men come forth; the Ethiopian and the Libyans, that handle the shield; and the Lydians, that handle and bend the bow.” Many writes have been said about the bravery of Ethiopians army in the ancient times. For instance Alemida said “they sit a horse well, are quiet strong and healthy and are brought up and insured to foil, enduring hunger and thirst as much as can be imagined, and continue in the field for the greater part of the year, suffering all the discomfort and inclemency of sun, cold, rain and with little food. Marco Polo also said, “you must know that in the province of Abash, there are excellent soldiers, and many horsemen. They have great number of horses. And it is well for them that this is so, for they have to fight with Sultan of Aden (Adal), with that of Nubia, and with many more besides. On account of this constant practice in arms, they are deemed the best soldiers of all the provinces of India.

The Yemeni Ambassador Hasen Bin Ahmed described “a people of great bravery, strong endurance, great numbers and a wide boundaries who could endure long journey and much suffering.”

Once again the Greek travelers and historians from ancient times provide us most helpful guide. They have left us very credible details of how their gods love the blameless Ethiopians, the whereabouts of this stupendous nation and the people.

Ethiopia’s civilization probably reached its apogee during the Axumite period and in the latter 3rd century Mani wrote that Aksum was known as one of the four great powers of the world. Cosmas Indicoplestes who was in the 6th century refers constantly to “Ethiopia” and its capital “Aksum”. He tells us of the export from Ethiopia of nuggets of Gold, Ivory and species, Myrrh and others where obtainable at the market of Adulis and Aksum. Aeschylus also said about this land and its people as "...a land far off, a nation of black men... men who live hard by the fountain of the sun where is the river of Ethiopia."

As Professor Sergew Hable Selassie summarized in his book “The Ancient and Medieval History of Ethiopia”: in the very beginning this country which we call Ethiopia today was only part of the area known by the same name to the classical writers. These authors divided Ethiopia into two parts and this distinction was important because later the northern part was to become known as Nubia and the name Ethiopia was retained only for the region of the Axumite Empire. As mentioned in the first paragraph some foreigners used the term Abyssinia in the past, nevertheless, Ethiopians have been addressed themselves for centuries as Ethiopians.

Some Biblical scholars flagrantly disregarding the true meaning of the Bible and mislead others by distorting the true meaning of the Bible in terms of Ethiopia. In 1976 the American Bible Society has deliberately altered the term “Ethiopia” into “Sudan” in the Good News Bible. The Holy Synod of the Ethiopian Orthodox Church (EOC) strongly protested and denounced this malicious act. In response to the EOC the office of the United Bible Societies recognized the deliberate alteration made by the American Bible Society and assured that further reprints of the Good News Bible would be stopped. This kind of fabrication will continue and we Ethiopians have the responsibility to defend our history and heritage.

***“Ethiopians shall bow down before him, and his enemies shall lick the dust.”*** **Psalm 72: 9**

Beide-Mariam Ejigu Retta

# መንፈሳዊ ግጥም

## ዝምታ

ስቃይ ሃዘን ሁከት የበዛበት ቦታ ፣
በዚያች ቀራኒዮ በዚያች ጎልጎታ ፣
የተሰቀለበት የዓለሙ ጌታ ፣
በርከት ያለ ለቅሶ ጩኸትና ዋይታ ፣
የሰው ልጅ ኃጢአቱ እጅጉን በረታ።

የድፍረት ኃጥአት የመላበት ቦታ፣
ፍጡር ፈጣሪውን በጥፊ ሲማታ ፣
እርሱ ግን ዝም...ዝም አለ የኛ ጌታ።
ሁሉንም ታገሰ ሁሉን በዝምታ ፣
ስቃዩን ህማሙን ድንግል ተመልክታ ፣
ልቧ አልችል አላ ሃዘኗም በረታ ፣
አምርራ አለቀሰች እግሩ ስር ተደፍታ።

የሰው ልጅ ልብ በኃጢአት ተሞልታ፣
ሊሰጡት አልቻሉም ትንሽ እንኳ ፋታ፣
አጣድፈው ወሰዱት ወደ ጎልጎታ ፣
አንዴ እየታሰረ አንዴ እየተፈታ ፣
የአብርሃም አምላክ ለኛ ተንገላታ ፣
እርሱ ግን ዝም ... ዝም አለ የኛ ጌታ።
ራሱን በዘንግ ሲመታ ፣
ያቺ የእራት ምሽት ያቺ ፋሲካ ማታ ፣
ይሁዳ ሸጠው አንድም ሳያመነታ ፣
ሥጋውንና ደሙን ለሐዋርያት
        ሰጠ አንድ ባንድ በተርታ ፣
ለሰው ልጅ ሊሆነው አለኝታ መከታ ፣
መከራን ተቀበለ በልጁ አዳም ፈንታ።
መድኃኔዓለም መድህን የኛ ቤዛ አለኝታ ፣
እርሱ ግን ዝም ... ዝም አለ የኛ ጌታ።
ያደረገው ለኛ ያ ታላቅ ውለታ ፣
ጌታን እናምውነ ዘንድ ከልብ ሳናመነታ ፣
ራሱን መስዋዕት አድርጎ ሰጠን የኛ ጌታ ፣
ዓለምን ሊያድን ከመሰውር ቦታ ፣
በመስቀል ታረቀን የሰራዊት ጌታ።
ሞትን ድል አድርጎ ዲያብሎስን መታ ፣
በሞቱ ድህነትን ሰጠን የኛ ጌታ ፣
እናቅርብ ምስጋና እንዘምር በእልልታ ፣
የሚሳነው ለሌለው ለብርሃናት ጌታ።

ምትኩ ኃይሌ
ሐመረ ኖህ ሰንበት ት/ቤት

## እረኛው

አንድ ቀን በህልሜ
ደክሞኝ ተጋድሜ
አየሁ አንድ እረኛ
ያልሆነ ምንደኛ
ለበጉ ሲል ነፍሱን የሠጠ ዝነኛ
በለመለመው መስክ በጎቹን አስፍሮ
ከጋራ ከማማው ሲያያቸው በአንክሮ
ነጣቂ አንበሳ አድብቶበት ኖሮ
ሚወደውን በጉን ነጥቆ ወስደበት
አውራው ሲያዝ አይተው ሌሎቹም ሸሹበት
አልቻለም ሊተወው ወረደ ከማማው
ሮጠ ተከተለው ደረሰበት ያዘው
ሳይፈራ ታገለው ጥርሱን ፈለቀቀው
ላብና ደም ወጣ አፋጨ ፍትጊያው
እልህና ግሣት ሰልፋን አጋጋለው
ያ ጨካኝ አንበሳ በጥፍሩ
        ባጭሮ እራሱን አደማው
የረታው መዳፍን ነካክሶ አቆሰለው
ልጆቹስ መች ተኙ ጎኑን ቦጫጨቁት
እየተከተሉ እግሩን አነከቱት
ጀርባውን ተልትለው አጥንቱን አሥቀሩት
ዳሩ-ሳይጥል ሳያሸንፍ እረኛው አይወድቅም
ሳያጠፋ አያርፍም ሳይገድል አልሞትም
ወይነዶ እያልኩኝ እኔም ቀጠልኩ ህልሜን
ነገን ተመኘሁት ልናገር መቆሜን
ታረክ ተለወጠ
ያ በግ አመለጠ
ሳይቆም ፈረጠጠ
እየተንደረደረ ገባ ከሕይወት ጋጣ
ከአራቱ ወንዞች ሊረካ ሊጠጣ
ደግሞ ለሞት እራት ከዚህ ማን ሊወጣ
እረኛው ግን አለ እንደተታገለ
ትድናለህ ብሎ ለበጉ እንደማለ
ፍፃሜው ደረሠ አንበሳው ወደቀ
መንጋው ፈነደቀ ሰማይ ምድሩ ሳቀ
ያ ነጣቂ ጠላት በጣት ደም ታነቀ
ነገር ዳሩን ያዘ ሁሉም ቀዘቀዘ
ሰማዩም ፈዘዘ
እረኛው አወጀ ተፈፀመ አለ
ጉልበት ክንድም ዛለ
አንገት ዘንበል አለ
ወደቀ እንደጣለ
ሞተ እንደገደለ።

ከዲያቆን ትዝታው ሳሙኤል